የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ–ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

8th Year No. 26
ADDIS ABABA–2nd July, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፱/፲፱፻፺፬ ዓ·ም
ለረዥም ጊዜ ሳይረከሱ ከሚቆዩ ከካርቦን የተሠሩ ኬሚካሎች ብክለት መቆጣጠሪያ የስቶክሆልም ኰንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ............................................. ገጽ ፩ሺ፯፻፷፯

## CONTENTS

Proclamation No. 279/2002
The Stockholm Convention on Persistent Organic Pollutants Ratification Proclamation .................................... Page 1767

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፱/፲፱፻፺፬
### ለረዥም ጊዜ ሳይረከሱ ከሚቆዩ ከካርቦን የተሠሩ ኬሚካሎች ብክለት መቆጣጠሪያ የስቶክሆልም ኰንቬንሽንን ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለረዥም ጊዜ ሳይረከሱ ከሚቆዩ ከካርቦን የተሠሩ ኬሚካሎች ወለድ ብክለትን በሚመለከት የስቶክሆልም ኰንቬንሽን እ·ኤ·አ ሜይ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ የወጣ ስለሆነ፣

ይህንኑ ኰንቬንሽን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለረዥም ጊዜ ሳይረከሱ ከሚቆዩ ከካርቦን የተሠሩ ኬሚካሎች ወለድ ብክለት መቆጣጠሪያ የስቶክሆልም ኰንቬንሽን ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፸፱/፲፱፻፺፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ኰንቬንሽኑ ስለመጽደቁ</u>

ለረዥም ጊዜ ሳይረከሱ ከሚቆዩ ከካርቦን የተሠሩ ኬሚካሎች ወለድ ብክለት መቆጣጠርን በሚመለከት እ·ኤ·አ ሜይ ፳፪ ቀን ፪ሺ፩ የወጣው የስቶክሆልም ኰንቬንሽን ፀድቋል።

፫· <u>የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ኃላፊነት</u>

የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አግባብ ካላቸው የፌዴራል፣ የክልል፣ የከተማ መስተዳድር የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የስቶክሆልም ኰንቬንሽን በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

፬· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፭ ቀን ፲፱፻፺፬ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

### *PROCLAMATION NO. 279/2002*
### *A PROCLAMATION TO RATIFY THE STOCKHOLM CONVENTION ON PERSISTENT ORGANIC POLLUTANTS*

WHEREAS, the Stocholm Convention on Persistent Organic Pollutants was adopted on the 22nd day of May, 2001;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said convention at its session held on the 2nd day of July, 2002;

NOW, THEREFORE, in accordance with Articles 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This proclamation may be cited as "the Stockholm Convention on Persistent Organic Pollutants Ratification Proclamation No. 279/2002".

2. *Ratification of the Convention*

The Stockholm Convention on Persistent Organic Pollutants, adopted on the 22nd day of May, 2001, is ratified.

3. *Responsibility of the Environmental Protection Authority*

The Environmental Protection Authority is hereby authorized to take, in cooperation with the appropriate Federal, Regional and City Administration government organs, actions necessary to implement the Convention.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 2nd day July of 2002.

Done at Addis Ababa, this 2nd day of July, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 8001